የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 613/0083/14
ቀን/Date ነሐሴ 1 8 2014

የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
**በያሉበት፣**

ጉዳዩ:- **በታሪፍ ቁጥር 2207.1000 እና 2208.9090 የሚመደቡ እቃዎች ቀረጥና ታክስ ይመለከታል**፡፡

እንደሚታወቀዉ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የሚያስከትለዉን ጉዳት ለመቀነስ እንዲቻል የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/12 በ18/1/2012 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ለኮቪድ-19 በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ የሚያገለግሉ ዕቃዎች ከማንኛዉም ቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የፈቀደውን መሰረት በማድረግ በኮሚሽኑ በኩል በቁጥር 4/06.50/12 መጋቢት 19/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አስፈላጊው ሁኔታ ሲሟላ በAPC 421 እየተመዘገቡ ከማንኛዉም ቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲስተናገዱ ማሳወቃችን ይታወሳል፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር መኢ.30/7/3032 በ13/04/2014ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ከላይ እንደተገለጸው ለኮቪድ-19 መከላከያ እንዲውሉ ላልተወሰነ ጊዜ ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ ከተፈቀዱት እቃዎች ዉስጥ በታሪፍ ቁጥር 2207.1000 እና 2208.9090 የሚመደቡት እቃዎች በአገር ውስጥ በበቂ መጠን የሚመረቱ ስለሆነ መስከረም 1 ቀን 2014 ጀምሮ ተግባረዊ በተደረገው የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ መሰረት በማንኛው ሁኔታ ወደ አገር ሲገቡ ሙሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው መሆኑን የገለጸበትን ደብዳቤ ኮፒ አንድ ገጽ በማያያዝ ይህ ሸኚ ደብዳቤ ከኮሚሽኑ ወጪ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በጉምሩክ ተቀባይነት በሚያገኙ ሰነዶች ላይ ቀረጥና ታክስ መሰብሰብ ያለበት መሆኑን እናሳዉቃለን፡፡

በተጨማሪም በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል የተደረገው ማሻሻያ የሚጸናበት ቀን ያልተገለጸ በመሆኑ ከኮሚሽኑ በሸኚ ደብዳቤ ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ከተላለፈት ቀን ጀምሮ ተቀባይነት በሚያገኙ ሰነዶች ላይ እንዲሆን መደረጉን ሚኒስቴር መ.ቤቱ እንዲያውቀው የዚህ ደብዳቤ ግልባጭ ተደርጎለታል፡፡

ከሠላምታ ጋር

**ግልባጭ**:-

- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ህግ ተገዢነት ዘርፍ
- ለንግድ እቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ፖሊሲ ጥናትና ትንተና ቡድን
- ለታሪፍ አሠራርና ድጋፍ ቡድን
  **ጉምሩክ ኮሚሽን**
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር
  **አዲስ አበባ**



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia
ፖ.ሳ.ቁ. 2559

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No 09/230/ፇ/3032
ቀን / Date 13/4/2014

ለጉምሩክ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ስኳር ኮርፖሬሽን በስሩ በሚገኙ የመተሐራና ፊንጫ ስኳር ፋብሪካዎች የፋብሪካ ተረፈ ምርት የሆነውን ሞላሰስ በመጠቀም የተመረተ የቴክኒካል አልኮል በ2013 በጀት ዓመት 7,000 ኪሎ ሊትር በክምችት የሚገኝ ሲሆን በ2014 በጀት ዓመት የምርት ዘመን በሁለቱም የስኳር ፋብሪካዎች 18,404.25 ኪሎ ሊትር ኤታኖል ለማምረት ዕቅድ ይዞ ወደ ኦፕሬሽን የገባ በመሆኑ ለፋርማሲቲካልም ሆነ ለአልኮል መጠጥ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን በቂ የኤታኖል ምርት ማቅረብ የሚችል መሆኑን በመግለፅ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ የሚገባው የኤታኖል ምርት የሚቆምበት ሁኔታ እንዲመቻች ጠይቋል፡፡

በዚሁም መሰረት

| Tariff Item No. | Description of Items |
|---|---|
| 2207.1000 | Undenatured, ethyl alcohol of an alcoholic strength by volume of 80% vol or higher |
| 2208.9090 | Undenatured,75% ethyl alcohol |

የሆነ ኤታኖል ወደ አገር ውስጥ ሲገባ በ2017 ሃርሞናይዝድ ሲስተም ላይ በመመስረት በተሻሻለው እና ከመስከረም 01 ቀን 2014 ጀምሮ ተግባራዊ በተደረገው የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ላይ የተቀመጠው የታሪፍ ምጣኔ ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ:-

> ለስኳር ኮርፖሬሽን
> አዲስ አበባ